9ኛ ዓመት ቁጥር 14
9th Year No. 14

ባህር ዳር ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ/ም
Bahir Dar, 20th April, 2004

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State
in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

ፖ.ሳ.ቁ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 3.50
Unit price 3.50

ማውጫ	Content
አዋጅ ቁጥር 101/1996 ዓ.ም. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያና የአደጋ መከላከል ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ	Proclamation No. 101/2004 The Amhara National Regional State Food Security Program Coordination and Disaster Prevention Office Establishment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 101/1996 ዓ.ም.
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያና የአደጋ መከላከል ጽ/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ ስር በሰደደ ድህነትና የምግብ ዋስትና መታጣት አዘውትረው የሚጠቁትን አካባቢዎች ነዋሪ ህብረተሰብ ችግር ለዘለቄታው ለመቅረፍና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፕሮግራሞችን የሚያስፈጽም ብቁ አደረጃጀት መፍጠር በማስፈለጉ፣

ድህነትን ለመቀነስና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በክልሉ ውስጥ የሚታቀዱትን ልዩ ልዩ የልማት ፕሮጀክቶች እየተከታተለ የሚያስተገብርና አቀናጅቶ የሚመራም ሆነ በበላይነት የሚያስተባብር እንዲሁም የክልሉን ሕብረተሰብ ከተፈጥሮና ሰው ሠራሽ አደጋዎች ለመጠበቅ፣ የአደጋ መንስዔዎችን በማጥናት የሕብረተሰቡን የመከላከል አቅም የሚያጐለብትና አደጋ ለሚደርስባቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች አፋጣኝ እርዳታ የሚያደርስ አንድ ራሱን የቻለና የተጠናከረ አካል በሕግ መሰየም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

Proclamation No. 101/2004
The Amhara National Regional State Food Security Program coordination and Disaster prevention office Establishment Proclamation

WHEREAS, it is necessary to create an efficient Organization to implement programs enabling to ever alleviate the problem of the inhabitants who are frequently affected due to deep-rooted poverty and scarcity of food security in the National Region;

WHEREAS, it is found appropriate to designate in law an autonomous and strengthened body which is to follow, enforce, direct in integration and coordinate over various development projects planned in the Region with a view to reducing poverty and ensuring food security as well as to protect the population of Region from natural and man-made disasters, promote the protection capacity of the society through studying causes of disaster and get immediate relief to disaster affected parts of the society;

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የክልሉ ህገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ሥር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያና የአደጋ መከላከል ጽ/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 101/1996 ዓ.ም." ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

"አደጋ" ማለት የተወሰነ የሕብረተሰብ ክፍል ወይም የአንድ አካባቢ ነዋሪ ባልታሰበ የተፈጥሮ ወይም ሰው ሠራሽ ችግሮች ምክንያት የምግብና ሌሎች መሠረታዊ ፍላጐቶችን ለማሟላት ሳይችል ቀርቶ በዘወትር አኗኗሩ ላይ ቀውስ በመድረሱ ያለ ሌሎች እርዳታ ኑሮውን ሊቀጥል የማይችልበት ሁኔታ መከሠት ነው።

ክፍል ሁለት

ስለምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያና የአደጋ መከላከል ጽ/ቤት መቋቋም፣ ተጠሪነት፣ ዓላማ፣ ስልጣን፣ አደረጃጀትና አመራር

3. ስለጽሕፈት ቤቱ መቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያና የአደጋ መከላከል ጽ/ቤት /ከዚህ በኋላ ጽ/ቤቱ እየተባለ የሚጠራ/ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው የክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የጽ/ቤቱ ተጠሪነት ለገጠር ልማት ቢሮ ይሆናል።

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the power vested in it under the provision of Article 49 Sub-Article 3(1) of the Revised Constitution of the Region, hereby issues this proclamation.

Part One

General

1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State Food Security Program Coordination and Disaster Prevention Office Establishment Proclamation No. 101/2004."

2. Definition

Unless the context requires, otherwise in this proclamation:

"Disaster" means the development of a situation wherein a segment of the community or the population of a locality cannot any longer meet the need for food and other basic necessities due to unpredictable natural or man-made calamities, with its daily life thus falling into crisis which renders it unable to survive without assistance from others.

PART TWO

Establishment, Accountability, Objective Power, Organization and Management of Food Security Program Coordination and Disaster Prevention Office

3. Establishment and Accountability of the Office

1. The Amhara National Regional State Food Security Program Coordination and Disaster Prevention Office /herein after referred to as "The Office"/ is hereby established as an autonomous body of the Regional Government having its own legal personality as per this proclamation.
2. The Office shall be accountable to the Rural Development Bureau.

4. ዓላማዎች

ጽ/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. በአስከፊ የድህነት ችግር እና ሥር በሰደደ የምግብ ዋስትና መታጣት ሣቢያ በሚጠቁ የክልሉ አካባቢዎች የሚኖረውና በቋሚነት ለችግሮቹ የተጋለጠው ሕዝብ ድህነቱ በዘላቂነት እንዲወገድለትና የምግብ ዋስትናው እንዲረጋገጥለት ዘላቂ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ለማምጣት የሚካሄዱ ጥረቶችን ማስተባበርና መደገፍ::

2. የከፋ የድህነት ችግርና የምግብ ዋስትና መታጣቱ ጉልቶ በሚታይባቸው ስፍራዎች የሚከሰቱ አደጋዎችን መሠረታዊ መንስዔዎች በማጥናትና የተፈጥሮ አካባቢን መልሶ ለማቋቋም የሚደረጉ ሁለገብ ጥረቶችን ማገዝ::

3. ለአደጋ ሰለባዎች አስፈላጊውን የምግብና ሌሎች መሠረታዊ የኑሮ ፍላጐቶች ለማሟላት የሚያስፈልገው እርዳታ በወቅቱ መድረሱን ማረጋገጥ፣ ሕብረተሰቡን ከጥገኝነትና ከጠባቂነት መንፈስ ለማላቀቅ ይቻል ዘንድ አደጋ ሊያደርስ የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ የሚያስችል አቅምን አስቀድሞ ማጐልበት::

5. የጽ/ቤቱ መደበኛ አድራሻ

የጽ/ቤቱ መደበኛ አድራሻ በባህርዳር ከተማ ውስጥ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልሉ ውስጥ በሌሎች አካባቢዎች ቅርንጫፍ/ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁም ይችላል::

6. የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ለምግብ ዋስትናና ለድህነት ቅነሣ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚያገኘውን ፈንድ በአግባቡ እና በብቃት ያስተዳድራል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

4. Objectives

The Office shall have the following objectives pursuant to this proclamation:

1. Coordinate and support efforts undertaken to bring sustainable economic and social development in order to cause the elimination of poverty for ever and thereby ensure food security of the people who are constantly exposed to the problems in areas of the Region affected due to absolute poverty and deep-rooted scarcity of food security.

2. Support all-round efforts undertaken to rehabilitate the natural environment by studying fundamental causes of disaster occurred in areas where absolute poverty problems and scarcity of food security is obviously observed.

3. Ensure that the assistance necessary to meet the required food and other basic necessities for life get timely to victims of disasters; and so as to detach the community from the sprit of dependency and expectancy, develop right ahead a capacity enabling to reduce the damage that a disaster can cause.

5. Head Office

The regular address of the Office shall be in Bahir Dar, and may establish branch/coordinating Offices in the Region as deemed necessary.

6. Powers and Duties of the Office

The Office shall have the following powers and duties:

1. Administer, co-ordinate, follow up and control appropriately and efficiently the fund which it obtains for the implementation of programs of food security and of poverty reduction;

2. ድህነትን ለመቀነስና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ለሚያስችሉ የተለያዩ ተግባራት ፋይናንስ ነክና ሌሎች ድጋፎችን በመስጠት ተግባራቱ መንግስታዊ፣ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በብዙሃን ማህበራት አማካኝነት እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤

3. በክልሉ ውስጥ አደጋን ለመከላከል፣ ድህነትን ለመቀነስና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተቀረፁትን የእርዳታ ፕሮግራሞች ማስፈፀሚያ የሚያስፈልጉና ልማት ነክ ፕሮጀክቶችን ያስተባብራል፣ ከሚመለከታቸው ጋር በመሆን አፈፃፀማቸውን ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፤

4. የፌሚ መ/ቤቶችን ሥራ ያስተባብራል፣ ፕሮጀክቶች ተቀናጅተው እንዲዘጋጁ ያደርጋል፣ የማስፈፀሚያ ፈንድ ያፈላልጋል፣ ሃብት ያሰባስባል፣ የዕርዳታ ግኙትንና አስተዳደርን በሚመለከት የፌዴራል መንግስት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ከእርዳታ ሰጭ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት ይፈጥራል፤

5. በድህነት ቅነሣና በምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች የሚታቀፈውን ሕዝብ መረጃ ያደራጃል፣ በየጊዜው የምግብ ዋስትናው የሚረጋገጥለትንና ከድህነት የሚወጣውን ሕዝብ መረጃ ይይዛል፣ ይተነትናል፤

6. የድህነት ቅነሣና የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞች አፈፃፀምን አስመልክቶ ለለጋሽ እና አበዳሪ ድርጅቶች እንዲሁም ለክልሉ እና ለፌዴራሉ መንግስታት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፤

7. ፕሮግራሞቹን የሚመለከቱ የፖሊሲ ሃሣቦችን ያመነጫል፣ የክልሉን መንግስት ያማክራል፣ አላማዎቹንና ተግባራቱን ለህዝብ ያስተዋውቃል፤

8. አግባብ ካላቸው የክልሉ መንግስት አካላት ጋር በመተባበር አደጋ ሊመጣ የሚችልበትን ምክንያት አስቀድሞ ያጠናል፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና መሰል መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያሰራጫል፤

2. Cause the execution of various activities enabling to reducing poverty and ensuring food security through governmental, non-governmental and civic associations by providing finance related and other assistances;

3. Co-ordinate development related projects necessary for the execution of designed assistance programs with a view to preventing disaster, reducing poverty and ensuring food security in the Region; and evaluate as well as control the implementation of same together with those who are concerned;

4. Co-ordinate the activity of operating offices; cause projects get prepared being coordinated; search for execution fund; collect property and make a relation with donor organizations in accordance with directives to be issued by the Federal Government concerning assistance procurement and its administration;

5. Organize data of the population incorporated in poverty reduction and food security programs; maintain and analyze data of the population whose food security to be ensured as well as getting out of poverty in the course of time;

6. Submit periodic reports to donor and creditor organizations as well as to the Regional and Federal Government concerning the implementation of poverty reduction and food security programs;

7. Generate policy proposals related to the programs; advise the Regional Government; and promote its objectives as well as duties to the public;

8. Undertake priorly studies, in cooperation with appropriate organs of the Regional Government, on causes of disaster occurrence; collect and thereby distribute early warning and similar data to the concerned bodies;

9. በክልሉ ውስጥ አደጋ በሚከሰትበት ጊዜ የደረሰውን ጉዳት፣ መወሰድ የሚገባውን እርምጃና ለዚሁ የሚያስፈልገውን ድጋፍ በዝርዝር የሚያመለክት ዕቅድ ያዘጋጃል፣ ለክልሉ የሚደለደለው እርዳታ በትክክል ለተረጂዎች መድረሱን ይቆጣጠራል፣

10. ከፌዴራሉ መንግስት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ጋር መሠረታዊ የውል ሥምምነቶችን አድርገው በክልሉ ውስጥ እንዲሠሩ የተፈቀደላቸውን መንግስታዊ ያልሆኑ ዓለም አቀፍም ሆነ አገር አቀፍ እርዳታ ሰጭ ድርጅቶችና ሥልጣን ባለው አካል እውቅና የተሰጣቸው ክልል በቀል መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ሥራ ያስተባብራል፣ ስለሥራቸው አፈጻጸምና ብቃታቸው ለክልሉ መንግስትና ለፌዴራል አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ሪፖርት ያደርጋል፣

11. የድህነት ቅነሳና የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችንና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የአደጋ መከላከል ሥራዎችን ለማስፈጸም እገዛ የሚያደርጉ የተለያዩ የሥራ መመሪያዎችንና ማንዋሎችን አዘጋጅቶ ሲፈቀድለት በሥራ ላይ ያውላል፣

12. የሥራ እንቅስቃሴውን በሚመለከት በየጊዜው ለገጠር ልማት ቢሮ ሪፖርት ያቀርባል፣

13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

14. ዓላማዎቹን ለማስፈፀም የሚረዱና ከዚህ አዋጅም ሆነ ከሌሎች ሕጐች ጋር የማይቃረኑ ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

7. ድርጅታዊ አቋም

ጽ/ቤቱ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

1. የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ፣
2. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊና እንደአስፈላጊነቱ ምክትል ኃላፊዎች፣

9. Prepare detailed plans, which indicate the damages sustained, the measures to be taken and the necessary assistance, when a disaster occurs in the Region; and supervise that the assistance allocated to the Region gets exactly to the victims;

10. Co-ordinate the activity of those which are permitted to work in the Region upon having made basic contract agreements with the Federal Government Disaster Prevention and Preparedness Commission, non-governmental international as well as national donor organizations and non-governmental Regional indigenous organizations that are granted recognition by an authorized body; make a report to the Regional Government and the Federal Disaster Prevention and Preparedness Commission concerning their work performance and efficiency thereof;

11. Prepare and execute upon approval various work guidelines and manuals that are helpful for the implementation of activities of poverty reduction as well as food security programs and of early warning;

12. Submit a report regularly to the Rural Development Bureau regarding its activities;

13. Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

14. Carryout related functions that are consistent with this proclamation as well as other laws and helpful for the implementation of its own objectives.

7. Organizational Structure

The Office shall have the following bodies:

1. Disaster Prevention and Preparedness Committee;
2. Office Head and as may be necessary a deputy Head;

3. የበታች የሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች አስፈላጊ ሠራተኞች::

8. ስለጽ/ቤቱ አመራር

1. ጽ/ቤቱ በጽሕፈት ቤት ኃላፊ ይመራል፣ ይተዳደራል::

2. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለገጠር ልማት ቢሮና ለርዕሰ መስተዳድሩ ይሆናል::

9. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባራት

የጽ/ቤቱ ኃላፊ ከዚህ በታች የተመለከቱት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ሥር የተጠቀሱትን የጽ/ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

2. የዓመቱን የሥራ ዝርዝርና የበጀት ድልድል አዘጋጅቶ ለክልሉ መንግስት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

3. ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣ በሥራ ላይ መዋሉንም ይቆጣጠራል፤

4. የምግብ ዋስትና፣ የአደጋ ተጋላጭነትና የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሥራዎችን በሚመለከት የጥናትና ምርምር ተግባር እንዲከናወን፣ የስታትስቲክስ መረጃዎች እንዲሰበሰቡና እንዲቀነባበሩ በማድረግ ለክልሉና ለፌዴራሉ መንግስት አካላት ያስተላልፋል፤

5. በልዩ ልዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች የሚሰተፉ የከፍተኛ ባለሙያዎች ቅጥርና አስተዳደር የሚፈፀምበትን መመሪያ ከለጋሽና አበዳሪ መንግስታትና ድርጅቶች ጋር የሚገቡ ውሎችና ስምምነቶችን መሠረት አድርጉ የገጠር ልማት ቢሮ የሚያወጣለት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽሕፈት ቤቱን ሌሎች ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በክልሉ ሲቪል ሠርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ያሰናብታል፤

3. Subordinate Heads and other necessary staff.

8. Management of the Office

1. The Head of the Office shall direct and administer the Office.

2. The Head of the Office shall be accountable to the Rural Development Bureau and the Head of the Government.

9. Powers and Duties of the office

The Head the Office shall have detailed powers and duties indicated herein under:

1. Direct and co-ordinate over the activities of the Office mentioned under Article 6 of this proclamation;

2. Prepare and submit the annual work details and budget allotment to the Regional Government and implement same up on approval;

3. Effect financial expenditure in accordance with the approved budget and work program of the Office and thereby supervise the implementation of same;

4. Cause the undertaking of researches, gathering and systematizing statistical data regarding activities of food security, vulnerability to disaster as well as of early warning and thereby send same to the Regional and Federal Government bodies;

5. Without limiting to the fact that the Rural Development Bureau to be issuing a directive, based on contracts and agreements made with donor and creditor governments and organizations, by which recruitment and administration of higher professionals be executed, employ, administer and dismiss other employees and supporting staff of the Office in accordance with the Civil Service Law of the Region;

6. ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ጽ/ቤቱን ይወክላል፤

7. ለሥራ ቅልጥፍና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ሥልጣንና ተግባሩን ለበታች የስራ ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

8. ስለሚያከናውናቸው ተግባራት ለገጠር ልማት ቢሮ የሥራ ዘገባ ያቀርባል።

10. የምክትል ጽ/ቤት ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር

የጽ/ቤቱ ምክትል ኃላፊ ተጠሪነቱ ለጽ/ቤቱ ኃላፊ ሆኖ፡-

1. በጽ/ቤቱ ኃላፊ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

2. የጽ/ቤቱ ኃላፊ በማይኖርበት ወይም ሥራውን ለማከናወን በማይችልበት ጊዜና ሁኔታ እርሱን ተክቶ ይሠራል።

ክፍል ሦስት

የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴ አወቃቀር፣ ተጠሪነትና ሥልጣን

11. የኮሚቴው አባላት አሰያየምና ተጠሪነት

1. ኮሚቴው ሰብሳቢውን ጨምሮ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚሰየሙ አባላት ይኖሩታል፣ ቁጥራቸውም እንደአስፈላጊነቱ ይወሰናል።

2. የኮሚቴው ተጠሪነት ለብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ርዕሰ-መስተዳድር ይሆናል።

3. የኮሚቴው ሴክሬታሪያት በጽ/ቤቱ ይሆናል።

12. የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር

ኮሚቴው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

6. Represent the Bureau in all its relations with third parties;

7. Delegate, upon representation, his powers and duties to subordinate Heads whenever it finds necessary for the efficiency of its activities;

8. Submit performance report to the Rural Development Bureau regarding the functions it discharges.

10. Powers and Duties of the Deputy Head of the Office

The Deputy Head of the Office being accountable to the Head of the Office shall:

1. Carry out duties specifically entrusted to him by the Head of the Office.

2. Perform, in the capacity of the Head of the Office, in case of absence or inability of the latter to discharge his duties.

PART THREE

Structure, Accountability and Power of Disaster Prevention and Preparedness Committee

11. Designation and Accountability of Members of the Committee

1. The Committee including the chairperson shall have members designated by the Council of the Regional Government, and their number shall be determined as deemed necessary.

2. The Committee shall be accountable to the Head of the National Regional Government.

3. The address of the Secretariat of the Committee shall be in the Office.

12. Powers and Duties of the Committee

The committee shall have the following powers and duties:

1. የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ብሔራዊ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፤

2. በክልሉ ውስጥ አደጋ የተከሰተባቸው ሥፍራዎች በይፋ እንዲገለፁ ያደርጋል፤

3. የዕርዳታ ፕሮግራሞችን በመገምገም አደጋ ለደረሰባቸው አካባቢዎች የተፋጠነ የዕርዳታ ወጭ እንዲመደብ ያደርጋል፤

4. የዕርዳታ ፕሮግራሞች የአደጋ መሠረታዊ መንስዔዎችን በማስወገድና ቀጣይነት ላለው የኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ አተኩረው እንዲንቀሳቀሱ ይሠራል፤

5. በልማት መስኮች ውስጥ የአደጋ መከላከል ፕሮግራም ተገቢው ትኩረት እንዲሰጠው ያደርጋል።

13. ስለ ኮሚቴው ስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት

1. ኮሚቴው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማናቸውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል።

2. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።

3. የኮሚቴው ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ኮሚቴው የራሱን ዝርዝር የስብሰባና ውስጣዊ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መወሰኛ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

14. ስለበታች ኮሚቴዎች መቋቋምና ተግባር

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ከክልል አቀፉ ኮሚቴ በተጨማሪ የበታች አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚቴዎች በየደረጃው ይቋቋማሉ።

1. Follow up and ensure the implementation of the National Disaster Prevention and Preparedness policy in the Region;

2. Cause the official declaration of disaster affected areas in the Region;

3. Cause, by evaluating assistance programs, the allocation of prompt assistance expenditure to disaster affected areas;

4. Work with a view to causing assistance programs operate emphasizing on the elimination of root causes of disaster, and thereby contribute for sustainable economic development;

5. Cause that disaster prevention program is given due attention in the filed of development.

13. Meeting and Decision Making Procedure of the Committee

1. The Committee shall hold a regular meeting twice a year; provided, however, that it may hold an extra ordinary meeting at any time when necessary.

2. The presence of more than half of members of the committee shall constitute a quorum.

3. Decisions of the committee shall be passed by simple majority vote. However, in case of a tie the chairperson have a casting vote.

4. Without prejudice to the provisions of this Article, the committee shall issue its own detailed internal rules and meeting procedures.

14. Establishment and Duties of Subordinate Committees

1. In addition to the Region-wide committee, there shall be established, pursuant to this proclamation, subordinate committees at each level for Disaster Prevention and Preparedness.

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተጠቀሱት ኮሚቴዎች በየተቋቋሙበት እርከን ኃላፊነታቸውን በመወጣት ረገድ ስለሚኖራቸው ሥልጣንና ተግባር ዝርዝሩ ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

ክፍል አራት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. የበጀት ምንጭ

የጽ/ቤቱ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የሚገኝ ይሆናል፦

1. በክልሉ መንግስት የሚመደብ በጀት፣
2. ከፌዴራሉ መንግስት የሚሰጥ ድጋፍ፣
3. ከዕርዳታ ሰጭና አበዳሪ አካላት የሚገኝ የዓይነትም ሆነ የጥሬ ገንዘብ ሃብትና
4. ሌሎች ምንጮች።

16. ስለ ሒሳብና የንብረት መዛግብት አያያዝ

1. ጽ/ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብትን ይይዛል።
2. የጽ/ቤቱ የሒሳብ መዛግብትና ገንዘብም ሆነ ንብረት ነክ ሠነዶች እንደሁኔታው በክልሉ ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ወይም በውጭ ኦዲተሮች ይመረመራሉ።

17. ስለ ፋይናንስና ንብረት አስተዳደር

ጽ/ቤቱ ከዕርዳታ ሰጭና አበዳሪ መንግስታትና ድርጅቶች በቀጥታ የሚያገኘውን ገቢ በሚመለከት የራሱን የዕቃ ግዥ፣ የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር መመሪያዎች አውጥቶ በገጠር ልማት ቢሮ ሲፀድቁለት በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል።

2. Particular of powers and duties of the committees stated under sub-Article 1 of this Article with regard to discharging their responsibilities at their level of establishment shall be determined by a regulation to be issued henceforth.

PART FOUR

Miscellaneous Provisions

15. Budget Sources

The Budget of the Office shall be drawn from the following sources:

1. Budget allocated by the Regional Government;
2. Support provided by the Federal Government;
3. Property obtained from donor and creditor bodies in kind or in cash; and
4. Other sources.

16. Keeping of Books of Accounts and Property

1. The Office shall keep complete and accurate books of accounts.
2. Documents of the Office shall be audited by the Office of the Auditor-General of the Region or by external auditors.

17. Administration of Finance and Property

The Office may issue guidelines of procurement, finance and property administration regarding the revenue that it directly obtains from donor and creditor organizations and thereby implement same upon approval by the Rural Development Bureau.

18. መብትና ግዴታን ስለማስተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር 9/1988 ዓ.ም. የተቋቋመው የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 9/1991 ዓ.ም. የተቋቋመው የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ወደ ተቋቋመው ጽ/ቤት ተላልፈዋል::

19. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

1. የሚከተሉት ሕጐች ተሽረው በዚህ አዋጅ ተተክተዋል:-

   ሀ. የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 9/1988 ዓ.ም.፣

   ለ. የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ክልል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 9/1991 ዓ.ም::

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ ወይም መመሪያ በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም::

20. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

የጽሕፈት ቤቱ አደረጃጀት በዚህ አዋጅ መሠረት ተቀርፆና በክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ፀድቆ በሥራ ላይ እስኪውል ድረስ የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 9/1988 ዓ.ም እና የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ክልል ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ደንብ ቁጥር 9/1991 ዓ.ም ተፈፃሚነታቸው ለሦስት ወራት ይቀጥላል::

21. ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን የማውጣት ሥልጣን አለው::

18. Transfer of Rights and Duties

Rights and duties of the Amhara National Regional State Disaster Prevention and Preparedness Commission established under proclamation No. 9/1995 as well as Rights and Duties of Food Security Program Co-ordination Office established under the Amhara National Regional State Executive Committee Regulation No. 9/1999 are hereby transferred to the Office established as per this proclamation.

19. Repealed and Inapplicable Laws

1. The following laws are hereby repealed and replaced with this proclamation:

   A) Disaster Prevention and Preparedness Commission Establishment Proclamation No. 9/1995;

   B) Food Security Program Coordination Office Establishment Regional Executive Committee Regulation No. 9/1999.

2. Any law, regulation or directive inconsistent with this proclamation shall not be applicable on matters provided in this proclamation.

20. Transitional Provisions

Disaster Prevention and Preparedness Commission Establishment Proclamation No. 9/1995 and Food Security Program Coordinating Office Establishment Regional Executive Committee Regulation No. 9/1999 are due applicable for three months pending the organization of the Office is structured pursuant to this proclamation and implemented upon approval by the Council of the Regional Government.

21. Power to Issue Regulation

The Council of the Regional Government shall have the power to issue regulations necessary for the implementation of this proclamation.

22. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

በዚህ አዋጅ ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ለክልሉ ገጠር ልማት ቢሮ የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ጽ/ቤቱ ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

22. Power to Issue Directive

Without prejudice to the power vested in the Rural Development Bureau by various provisions of this proclamation, the Office may issue directives necessary for the execution of this proclamation and regulations to be issued pursuant to this proclamation.

23. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህርዳር
ሚያዝያ 12 ቀን 1996 ዓ.ም.

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

23. Effective Date

This proclamation shall come into force commencing the date of its publication in the *Zikre Hig Gazetta* of the Regional State.

Done at Bahir Dar,
This 20th day of April, 2004

Yosef Retta
President of the Amhara National Region